በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ
በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ዜና-መጽሔት ቁ.47
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Communication and International Relations Department
Bi-monthly News Letter No.47

# 5ኛው መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ሊካሄድ ነው

## .የኢትዮ-ቻምበር ፎረም በዕለቱ ይከናወናል

የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት 5ኛ መደበኛ ጠቅላላ ጉባኤ ጥር 28 ቀን 2005 ዓ.ም. በሂልተን ሆቴል ይካሄዳል፡፡

በተያዘው መርሀ-ግብር መሰረት ከቀኑ 8፡30 ጀምሮ የሚካሄደው ጠቅላላ ጉባኤ ሁሉም የክልሎችና የከተማ አባል ምክር ቤቶች ተወካዮች የሚገኙበት ሲሆን የንግድ ሚንስትሩ ክቡር አቶ ከበደ ጫኔ በእንግድነት ተገኝተው የመክፈቻ ንግግር በማድረግ የጉባኤውን በይፋ መከፈት ያበስራሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡

በመቀጠልም የጠቅላላ ጉባኤው አጀንዳ ቀርቦ ከፀደቀ በኋላ የምክር ቤቱ ፕሬዚዳንት ወ/ሮ ሙሉ ሰሎሞን የምክር ቤቱን የ2004ዓ.ም. የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡

በተመሳሳይ ሁኔታ የምክር ቤቱ የ2004ዓ.ም. በጀት ዓመት የሂሳብ መግለጫ ሪፖርትበውጭ ኦዲተር ይቀርባል፡፡ በመቀጠልም በሁለቱም ሪፖርቶች ላይ ጠቅላላ ጉባኤው ውይይት በማድረግ ያፀድቃል፡፡

ጠቅላላ ጉባኤው በሌሎች ጉዳዮች ላይ እንደሚወያይና ሊሰሩ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ መመሪያ ይሰጣል፡፡

ጠቅላላ ጉባኤው ከመካሄዱ በፊት በዕለቱ ከጠዋቱ 2፡30 ጀምሮ ሁሉም የጉባኤው አባላት በተገኙበት 3ኛው የቻምበር ፎረም በሂልተን ሆቴል ይካሄዳል፡፡

የ3ኛው የቻምበር ፎረም የውይይት አጀንዳ ተሻሽሎ በወጣው አዲሱ የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 769/2012 እና የማስፈፀሚያ ደንቡ ላይ ይሆናል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች የጥናት ፅሁፎች በኢንዱስትሪ ሚኒስቴርና በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ም/ቤት ይቀርባል፡፡

## ገቢዎችና ጉምሩክ የአንድ መስኮት አገልግሎት ለመስጠት ጥናት እያስጠና ነው

የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወ/ሮ ሙሉ ሰሎሞን ከአፍሪካ ኢንቨስትመንት ክላይሜት ዋና ኦፐሬሽን ኦፊሰር ሚካኤል ማካሌ ጋር በገቢ ንግድ በተለይ በጉምሩክና የወደብ አገልግሎት ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን ለመፍታት በታቀደው ሀገራዊ ፕሮጀክት ላይ



ተወያዩ፡፡

ዋና ኦፐሬሽን ኦፊሠሩ እንደተናገሩት ፕሮጀክቱ በገቢ ንግድ ላይ የሚታዩትን ችግሮች ለመፍታት ታስቦ የታቀደ ሲሆን የአፍሪካ ኢንቨስትመንት ክላይሜት ከኢትዮጵያ ገቢዎች እና ጉምሩክ ባለሥልጣን ጋር በመሆን ፕሮጀክቱን ለመተግበር ጥናት እያጠና መሆኑን ገልፀዋል፡፡

ፕሮጀክቱ የአንድ መስኮት አገልግሎትን በመዘርጋት እና የተለያዩ ተቋማትን በኔትዎርክ በማስተሳሰር ደንበኞች የተቀላጠፈ አገልግሎት እንዲያገኙ በማድረግ በገቢ ንግድ ላይ የሚታዩትን ችግሮች ለመቅረፍ ያግዛል ብለዋል፡፡

አድራሻ፡ስ፡ - +251-011-5517699
ኢ.ሜይል: ethchamb@ethionet.et
ደረ-ገጽ፡- www.ethiopianchamber.com

በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ
በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ዜና-መጽሔት ቁ.47
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Communication and International Relations Department
Bi-monthly News Letter No.47

በመንግስት፤ መንግስታዊ ባልሆኑ እና በፋይናንስ ተቋማት ውስጥ የሚገኙትን ከገቢ ንግድ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በአንድ ኔትዎርክ ውስጥ በማስገባት ተገልጋዮች የፈለጉትን መረጃ እና አገልግሎት ማግኘት እንደሚያስችላቸው ተናግረዋል፡፡

በሃገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄድ ትልቅ ፕሮጀክት እንደመሆኑ መጠን የተለያዩ ተቋማት የተቀናጀ ጥረት እና ድጋፍ እንደሚያስፈልግ የገለፁት ዋና ኦፕሬሽን ኦፊሰሩ በሰኔጋል ተመሳሳይ ችግር አጋጥሞ



እንደነበረ እና የተለያዩ ተቋማት ባሳዩት ያለሰለሰ ጥረት ሊፈታ መቻሉን አስታውሰዋል፡፡

የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት (ኢንዘማም) ፕሬዚዳንት ወ/ሮ ሙሉ ሰሎሞን በበኩላቸው በጉምሩክ እና ወደብ አገልግሎት ጋር በተያያዘ የሚታየውን ችግር ለመቅረፍ የአፍሪካ ኢንቨስትመንት ክላይሜት እያደረገ ያለውን ጥረት በማድነቅ ችግሩ የግል ዘርፉን በተለየ እየጎዳው እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

በጉምሩክ ዙሪያ ያሉት ችግሮች የተወሳሰቡ መሆናቸውን ገልፀው ችግሩን ለመፍታት ከመንግስት ከፍተኛ ባለስልጣናን ጋር የተለያዩ ውይይቶች መደረጋቸውን አስታውሰዋል፡፡

አድራሻፋክስ: - +251-011-5517699
ኢ.ሜይል: ethchamb@ethionet.et
ደረ-ገጽ:- www.ethiopianchamber.com

የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ጠንካራ የግል ዘርፍ እና ነፃ ኢኮኖሚ ለመፍጠር የተለያዩ ሥራዎችን እየሰራ እንደሆነ ገልፀው እስካሁን ያለው ሂደት አበረታች መሆኑን ተናግረዋል፡፡ ምክር ቤቱ ይህንን ሀገራዊ ፕሮጀክት ለማሳካት ከምን ግዜ በላይ ዝግጁ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

## አሴኮ ፖላንድ በኢትዮጵያ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ገበያ ለመሰማራት ፍላጎቱን ገለፀ

አሴኮ ፖላንድ በኢትዮጵያ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ዘርፍ ለመሰማራት ፍላጎት እንዳለው እና ጠንካራ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ኩባንያ ለመክፈት ማቀዱን ገለፀ፡፡

ይህ የተገለፀው የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸሃፊ አቶ እንዳልካቸው ስሜ ከፖላንድ አምባሳደር በኢትዮጵያ ጃሴክ ጃንኮውስኪ እና የአሴኮ ፖላንድ ሱፐርቫይዘርይ ቦርድ አባል ዳርየስዝ ብርዜስኪ በሁለቱም ሃገራት መካከል ያለውን የንግድ እና ኢንቨስትመንት ሁኔታ እና አሴኮ ፖላናድ ኢትዮጵያ ውስጥ ኢንቨስት በሚያደርግበት ሁኔታ ውይይት በተደረገበት ወቅት ነው፡፡

በዚሁ ጊዜ አምባሳደር ጃሴክ እንደተናገሩት የአውሮፓ ሃገራት በአፍሪካ የንግድ እና ኢንቨስትመንት ውስጥ ያላቸውን ድርሻ በሌሎች ሃገራት እየተተካ መምጣቱን ገልፀው በአውሮፓ እና አፍሪካ ሃገራት ያለውን የንግድ እና ኢንቨስትመንት ግንኙነት ይበልጥ ለማጠናከር ብዙ መስራት እንዳለበት ተናግረዋል፡፡

በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ
በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ዜና-መጽሔት ቁ.47
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Communication and International Relations Department
Bi-monthly News Letter No.47

አፍሪካ ተመራጭ የኢንቨስትመንት መዳረሻ እየሆነች መምጣትዋን የተናገሩት አምባሳደሩ የአውሮፓ ሃገራት አፍሪካ ውስጥ ያለቸውን የኢንቨስትመንት ድርሻ ለማሳደግ ትልቅ ፍላጎት እንዳላቸው ገልፀዋል፡፡

የአሴኮ ፖላንድ ሱፐርቫይዘርይ ቦርድ አባል ዳርየስዝ ብርዜስኪ በበኩላቸው አሴኮ ፖላንድ በኢትዮጵያ የኢንፎርሜሽን እና ኮሙኒኬሽን ዘርፍ ለመሰማራት እና በኢትዮጵያ ውስጥ ጥልቅ እና ጠንካራ የሆነ የኢንፎርሜሽን እና ኮሙኒኬሽን ኩባንያ ለመመስረት ፍላጎት እንዳለው ገልፀዋል፡ ፡



ኢትዮጵያ ውስጥ የሚመሰረተው ኩባንያ አሴኮ ፖላንድ ምርቶቹን እና አገልግሎቶቹን በሌሎች የአፍሪካ ሃገራት ለማስገባት ለሚያደርገው ጥረት ትልቅ እገዛ ያደርጋል ብለዋል፡፡ አሴኮ በአውሮፓ ውስጥ ትላልቅ ከሚባሉት የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ኩባንያዎች አንዱ መሆኑን ያስረዱት ሚስተር ዳርየስዝ ኩባንያው በተለያዩ የአለማችን ክፍሎች በአሜሪካ፣ ካናዳ፣ እስራኤል ጨምሮ የተለያዩ ፕሮጀክቶችን እያካሄደ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

የኢትዮጵያ የንግድ እና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ምክትል ዋና ጸሃፊ አቶ እንዳልካቸው ስሜ በበኩላቸው ኢትዮጵያ በፍጥነት እያደጉ ካሉት የአለማችን ሃገራት አንዷ መሆንዋን ጠቅሰው ላለፉት ስምንት ዓመታት ባለ ሁለት አኃዝ የኢኮኖሚ እድገት ማስመዝገብዋን ተናግረዋል፡፡ ምክትል ዋና ጸሃፊው አክለውም ሃገሪትዋ ያስመዘገበችውን የኢኮኖሚ እድገት ለማስቀጠል የግሉ ዘርፍ እና የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ በኢኮኖሚው ውስጥ የጎላ ሚና እንዲጫወቱ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራበት እንደሚገኝ ገልፀዋል፡፡

የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ ንግድንና ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት ወሳኝ ሚና እንዳለው የተናገሩት ምክትል ዋና ፀሃፊው ኢትዮጵያ እየተገበረችው ባለችው የአምስት አመት የእድገት እና ትራንስፎርሜሽን ዕቅድ ላይም ትልቅ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል አንዱ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡

አሴኮ በኢትዮጵያ የኢንፎርሜሽን ኮሙንኬሽን ዘርፍ ቢሰማራ ተጠቃሚ ሊሆን እንደሚችልም ገልፀውላቸዋል፡፡

---

## በምክር ቤቶች የአባልነት ተግዳሮቶች፣ የተሻለ አገልግሎት መሥጠት በሚል ርዕሰ ጉዳይ አውደ ጥናት ተካሄደ

---

ሳይፕ የተሰኘ አለም አቀፍ ተቋም የንግዱ ማኅበረሰብ በምክር ቤቶች ላይ ያለውን ተሳትፎ እንዲሁም ምክር ቤቶች ለንግዱ ህብረተሰብ የተሻለ አገልግሎት እንዴት መስጠት ይችላሉ? ርእሰ ጉዳዮች ዙሪያ ያዘጋጀውን የጥናት ፅሁፍ ረቂቅ ለማጎልበት የሚያስችለውን የውይይት መድረክ አዘጋጀ፡፡

የክልሎችና የከተሞች የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤቶች ፕሬዚዳንቶችና ዋና ፀሐፊዎች እንዲሆም የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት የማኔጅመንት አባላት በተገኙበት የመግቢያ ንግግር ያደረጉት የሳይፕ በኢትዮጵያ ስራአስኪያጅ አቶ ኃይለመለኮት አስፋው በኢትዮጵያ በመቶ ሺኅ የሚቆጠሩ የንግዱ ማኅበረሰብ አባላት የሚገኙ ሲሆን በንግድ ምክር ቤቶች አባልነት የታቀፉት ግን ከ10 በመቶ እንደማይነልጡ

በኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት
የኮሙኒኬሽንና ዓለም አቀፍ ግንኙነት መምሪያ
በየ15 ቀኑ የሚዘጋጅ ዜና-መጽሔት ቁ.47
Ethiopian Chamber of Commerce and Sectoral Associations
Communication and International Relations Department
Bi-monthly News Letter No.47

ተናግረዋል፡፡

እንደሳይት ጥናት ከነዚህ ውስጥም በምክር ቤቶች ውስጥ ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉት ቁጥር በእጅጉ ያነሰ ነው፡፡

የሳይት ጥናት በዚህ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን የችግሩን መፍትሄ ለመረዳት ቃለ መጠይቆች አዘጋጅቶ በየክልሉ በመዘዋወር ጥናት ያደረገ ሲሆን በተገኘው ውጤት በርካታ የሚሆኑት የንግዱ ማኅበረሰብ አባላት ስለምክር ቤቶች አገልግሎት፣ አባል በመሆን የሚያስገኘው ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች ግንዛቤ የሌላቸው መሆኑን ለመረዳት ተችሏል፡፡



የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ወ/ሮ ሙሉ ሰሎሞን በዕለቱ ተገኝተው ባደረጉት የመክፈቻ ንግግር ሳይት ለውይይት ይዞ የቀረበው የጥናት ፅሁፍ በእጅጉ ጠቃሚ መሆኑን አወድሰው ምክር ቤቶች ካሉባቸው ዋና ዋና ችግሮች አንዱ የአባላት ውሱንነት መሆኑን አበክረው ተናግረዋል፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎን ምክር ቤቶች እርስ በእርሳቸው በመተጋገዝ እና ልምዶችን በመለዋወጥ የሚያጋጥመሟቸውን ተግዳሮቶች በጋራ ለመፍታት በመፈቃቀርና በመተሳሰብ መጓዝ እንደሚገባ አስገንዝበዋል፡፡

በተጨማሪም ከክልሎች የተወጣጡ የሴቶች ማኅበራት በክልሎቻቸው እያደረጉ ስለሚገኘው ዘርፈ ብዙ ተግባራት ገለፃ ያደረጉ ሲሆን በመጨረሻም በሳይት ረቂቅ የጥናት ፅሁፍ ላይ የተለያዩ አስተያየቶች ቀርበው ውይይቱ ተጠናቋል፡፡

## ዜና ፎቶ



(ከታች )ከሳይት አውደ ጥናት በከፊል





አድራሻፋክስ: - +251-011-5517699
ኢ.ሜይል: ethchamb@ethionet.et
ደረ-ገጽ፡- www.ethiopianchamber.com